# በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት

# የስነ-ሕዝብ ምክር ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአፈጻጸም መመሪያ

ህዳር 2002 ዓም

<u>ሀዋሣ</u>

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

1.1 መግቢያ ------------------------------------------------------------------------------------1

1.2 ዓላማ ---------------------------------------------------------------------------------------2

1.3 አስፈላጊነት -----------------------------------------------------------------------------2

## ክፍል ሁለት

2. ብሄራዊ የስነ-ሕዝብ ፖሊሲ ይዘት ---------------------------------------------------------------3

2.1 የስነ-ሕዝብ ፖሊሲ ዓላማ አስፈላጊነት ዓላማና ግቦች--------------------------------------3

## ክፍል ሦስት

3.የስነ-ሕዝብ ም/ቤት አወቃቀር፣ተግባርና ሀላፊነት--------------------------------------------------7

3.1 የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አወቃቀር ---------------------------------------------------------------7

3.2 የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ተግባርና ሀላፊነት ----------------------------------------.--------7

3.3 በዞኖች/ በሀዋሣ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ም/ቤት አወቃቀር------------------8

3.4 የዞኖች/የሀዋሣ ከተማ አስ/ር የሥነሕዝብ ም/ቤት ተግባርና ኂላፊነት----------------------9

3.5 በልዩ ወረዳ ፣በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተማ ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ም/ቤት አወቃቀር.10

3.6 በልዩ ወረዳ፣በወረዳና በከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተማ ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ም/ቤት ኃላፊነትና ተግባር….10

## ክፍል አራት

4.የስነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር፣ተግባርና ሀላፊነት ------------------------------------12
4.1 የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ -------------------------------------------------------------12
4.1.1 የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር-----------------------------------12
4.1.2 የክልሉ የሥነሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት-------------------------12
4.2 የዞንና የሀዋሣ ከተማ አስ/ር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር
ተግባርና ሃላፊነት----------------------------------------------------------------------13
4.2.1 የዞንና የሀዋሣ ከተማ አስ/ር የሥነሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር-----------13
4.2.2 የዞንና የሀዋሣ ከተማ አስ/ር የሥነሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር-14
4.3 የልዩ ወረዳ/የወረዳ /ከተማ አስ/ር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር----15
4.3.1 የልዩ ወረዳ/የወረዳ/ከተማ አስ/ር የሥነሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር---------15
4.3.2 የልዩ ወረዳ/ወረዳ/ከተማ አስ/ር የሥነሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር..........15

## 1.1 መግቢያ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በ13 ዞኖች፣በ8ልዩ ወረዳዎች፣ በ22 የከተማ አስተዳደሮች፣በ126 ወረዳዎችና 3927 ቀበሌዎች የተዋቀረ ሲሆን በ1999 ዓ.ም በተካሄደው ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት 15.04 ሚሊዮን ሕዝብ ሲኖረው ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ 20% ይሿል።

ክልሉ 110,932 ስ.ኪ. ሜትር ስፋት በመያዝ ከአገሪቱ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 10% የያዘ ነው።

ሕዝብ ለአንድ አገር ልማት ወሳኝ ሀይል መሆኑ ባይካድም ከኢኮኖሚና ማነበራዊ ዕድገት ጋር የማይመጣጠን ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ግን የልማት ሀይል መሆኑ ቀርቶ የልማት ስጋት መሆኑ ዕውን ነው። ከዚህ አንፃር መንግሥት በተቀናጀና በተፋጠነ ሁኔታ የአገሪቱን ልማት ለማሣደግ እንዲረዱ ካወጣቸው በርካታ ፖሊሲዎች መካከል አንዱ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ነው።

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የፋ/ኢ/ል/ቢሮ የስነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ፖሊሲውን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል።

ከነዚህ ውስጥ የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች ማቋቋምና የ3 እና የ5 አመት የስነ-ሕዝብ ኘሮግራም ዶክመንቶች አዘጋጅቶ በሴ/ር መ/ቤቶች የልማት ዕቅዶች ውስጥ ተካተው ተግባራዊ አድርጓል። በማድረግ ላይም ይገኛል።

ስነ-ሕዝብ በባህሪው ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ መጠን የስነ-ሕዝብ ጉዳይ በአንድ መ/ቤት ወይም ተቋም የተናጥል እርምጃ ብቻ የሚፈታ ሳይሆን የተለያዩ ሴ/ር መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የተባበረና የተቀናጀ ጥረት የሚጠይቅ አብይ የልማት አጀንዳ ነው። በመሆኑም በክልላችን የስነ-ሕዝብ ሥራዎችን በበላይነት የሚያስተባብርና የሚመራ የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና ከተለያዩ ሴ/ር መ/ቤቶች ድርጅቶችና ተቋማት ተውጣጥቶ ለሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚሰጥ የቴክኒክ ኮሚቴ ቀደም ሲል በተቋቋመባቸው የአስተዳደር እርከኖች አጠናክሮ ለመቀጠል ባልተቋቋሙባቸው ደግሞ በአዲስ መልክ ለማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ይህ መመሪያ 5 ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ፣አላማና አስፈላጊነትን ይሿል። ክፍል ሁለት ከሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አንፃር የሴ/ር መ/ቤቶችን ሚና የሚያስቃኝ ሲሆን በክፍል ሦስትና አራት የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር ፣ተግባራትና

ሀላፊነትን በቅደም ተከተል አካቷል፡፡ በመጨረሻው ክፍል የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ተግባርና ሃላፊነቱን የሚተነትነው ክፍል ይገኛል፡፡

## 1. 2 ዓላማ

የሥነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴ የማቋቋሚያና የአፈጻጸም መመሪያ አጠቃላይ ዓላማ የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴን በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች ማቋቋምና የሚሠሩትን ተግባራትና ሀላፊነት በግልጽ ለማሳየት የሚረዳ ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት ፡-

- በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ ከተማ አስተዳደርና በወረዳ ደረጃ የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ከሚቴ ለማቋቋም እንደ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል ፣
- በየደረጃው የሚቋቋሙ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴዎች የሚያከናውኑአቸውን ተግባራትና ሀላፊነት በዝርዝር ያመለክታል፣
- የስነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት በየደረጃው ከሚቋቋሙት የሥነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት በግልጽ ማሳየት ናቸው፣

## 1.3 የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ቴክኒክ ኮሚቴ አስፈላጊነት

የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊነት የሆነበት ምክንያት

- ከዚህ በፊት የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴን በየደረጃው ለማቋቋምና የሚያከናውኗቸውን ተግባራትና ሀላፊነት በዝርዝርና በግልጽ የሚያሳይ የአፈጻጸም መመሪያ ያልነበረ በመሆኑ፣
- በየደረጃው ተቋቁመው የነበሩት የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ለማቋቋምና የሚያከናውኑትን ተግባርና ሀላፊነት የሚያሣይ የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣
- በክልሉ በየደረጃው የሚገኙ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ ሴ/ር መ/ቤቶችና ድርጅቶች መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግበራ በማካሄድ ላይ ስለሆኑ የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ተግባርና ሀላፊነት ከዛ አንፃር ቃኝቶ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ነው፡፡

## *<u>ክፍል ሁለት</u>*

### 2. <u>የብሔራዊ ሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ይዘት</u>

#### 2.1 <u>የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ዓላማና ግቦች</u>

##### 2.1.1 <u>የፖሊሲው አስፈላጊነት፣</u>

በምጣኔ ሀብትና ማኅበራዊ ልማት ዕድገትና በፍጥነት እየጨመረ በሚገኘው የሕዝብ ቁጥር መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ለማጥበብ ከተነደፉት ብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አንዱ በ1985 ዓ.ም ይፋ የሆነውና በመተግበር ላይ የሚገኘው የብሔራዊ ሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ነው።

ብሔራዊ ሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ይፋ ሆኖ ተግባራዊ እንዲሆን ካደረጓቸው ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መኖርና በሌላ በኩል ደግሞ ዝቅተኛ ምርትና ምርታማነት በግብርናው፣በኢንዱስትሪውና በአገልግሎት ዘርፍ መኖር ናቸው። ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር የማይጣጣምና ዝቅተኛ ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መኖር በክልሉ ብሎም በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ፤ከፍተኛ የእናቶችና የሕፃናት ሕመምና ሞት እንዲሁም ዝቅተኛ አማካይ የዕድሜ ጣሪያ እንዲኖር ተፅዕኖ አደፊሯል።

ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ዘርፈ-ብዙ የሥነ-ሕዝብና ልማት ችግሮችን በሂደት ለመቅረፍና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ በመለወጥ ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል ፖሊሲው ወሳኝ ሚና አለው። በመሆኑም ፖሊሲው በጥቅሉ ሲታይ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ልማት በማፋጠን፣ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ዋና ምክንያት የሆነውን የውልደት መጠን ደረጃ በደረጃ በመቀነስ በአዝጋሚ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ በሚገኘው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መካከል ያለውን ክፍተት በማጥበብ፣ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የኑሮ ደረጃ በማሻሻልና በቀላሉ ለአደጋ ተጋላጭ የሚሆኑትን የእናቶች፣ የሕፃናትንና የልጆችን ሕመምና ሞት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ዘላቂ ልማትን እውን ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳል።

## 2.1.2 ዓላማ

የብሔራዊ ሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ዋና ዓላማ በሀገሪቱም ሆነ በክልሉ እየታየ ያለውን ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከልማት ዕድገትና ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር የተመጣጠነ የሕዝብ ዕድገት እንዲኖር በማድረግ በቀጣይነት አሁን ያለውን አስከፊ ድህነት ደረጃ በደረጃ በመቀነስ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ነው፡፡

የፖሊሲውን ዓላማ ለማሳካትና ከዳር ለማድረስ በፖሊሲ ሠነድ ውስጥ የተመለከቱት አጠቃላይና ዝርዝር ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 2.1.3 ግቦች

- በዝቅተኛ የምጣኔ ሀብት ዕድገትና በከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መሃል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ የሕዝብ ቁጥርን በዕቅድ መቀነስና የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን፣
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት መቀነስ፣
- የተፈጥሮ አካባቢን በዘላቂነት ለመጠበቅ የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የሴቶችን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማስወገድ የሴቶች የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሣትፎቸውን ማሣደግ፣
- ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑትን የኀብረተሰብ ክፍሎች ማለትም የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የሕፃናትንና አረጋውያንን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ማሻሻል ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ግቦች አሉት፡-

- የእያንዳንዷ ሴት አማካይ የውልደት መጠን በ2015 ዓ.ም ወደ 4 ዝቅ እንዲል ማድረግ፣
- የጽንስ መከላከያ ዘዴ ተጠቃሚነት ሽፋንን በ2015 ዓ.ም ወደ 44% ከፍ እንዲል ማድረግ፣
- የእናቶችን፣የሕፃናትንና የልጆችን ሕመምና ሞት መጠኑን መቀነስና የሕዝቡን ደህንነት ማሻሻል፣
- በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሴቶች ተሣትፎ እንዲጨምር ማድረግ ፣

- በማናቸውም የኢኮኖሚና ማኀበራዊ መብቶች፣የንብረት ባለቤትነት የሥራ ዕድልን ጨምሮ የሴቶችን ሙሉ ተጠቃሚነት የሚገረሩ ድንጋጌዎችና ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ፣
- የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅና የልማት ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ሚዛናዊ የሕዝቦች ያሰፋፈር ሥርጭት መኖሩን ማረጋገጥ፣
- ለግብርናው ዘርፍ ያለውን ምርታማነት መጨመርና የሥራ ዕድልን የሚፈጥሩ ሌሎች ከግብርና ውጭ የሆኑ ሥራዎችን ማስፋፋት፣
- ስለተመጠነ ቤተሰብ ጥቅም ከአጠቃላይ የሰው ልጅ ደህንነትና ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ሀገር አቀፍ የሕዝብ ነክ ኢንፎርሜሽን ፣ የትምህርትና የቅስቀሳ መርሐ-ግብርን ማካሄድ ናቸው፡፡

# *<u>ክፍል ሦስት</u>*

## 3. የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አወቃቀር ፣ተግባርና ኃላፊነት

### 3.1 <u>በክልል ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አወቃቀር</u>

የክልል ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚመራ ሲሆን የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ወሳኝ የሥራ ሂደት የሚገኝበት ፋ/ኢ/ል/ቢሮ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

<u>የክልል ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት</u>

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር - ሰብሳቢ
2. የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ - ፀሐፊ
3. የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ - አባል
4. የክልሉ የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መ/መ/ሴክሬታሪያት ኃላፊ -አባል
5. የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ - አባል
6. የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ኃላፊ - አባል
7. የክልሉ ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ - አባል
8. የክልሉ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ - አባል
9. የክልሉ ሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ሥራ አስኪያጅ - አባል
10. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ- አባል

11.የሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ ኘሬዝዳንት - አባል

12. የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኀበር ደቡብ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ - አባል

13.የክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባዔ- አባል

14.የክልሉ ብ/ሰቦች ም/ቤት አፈ-ጉባዔ አባል

15.የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ/የሲዳማ ሀገረ ስብከት ሊቀ-ጳጳስ -አባል

16.የክልሉ የአብያተ-ክርስትያናት ህብረት ሊ/መንበር - አባል

17.የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤ/ክርስትያን የደቡብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል

18.የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት የደቡብ ቅርንጫፍ ኃላፊ - አባል

19.የሀዋሪያት ቤ/ክርስቲያን የደቡብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል

20.የተቀናጀ የቤተሰብ ጤና አገልግሎት ደቡብ ቅርንጫፍ ኃላፊ - አባል

21.አይ ፖስ ኢትዮጵያ ደቡብ ቅርንጫፍ ኃላፊ -አባል

22.ኢንጀንደር ሄልዝ ደቡብ ቅርንጫፍ ኃላፊ -አባል

23.ኤፍ.ኤች.አይ ደቡብ ቅርንጫፍ ኃላፊ - አባል

24.የክልሉ ወጣቶች ፌዴሬሽን ኘሬዝዳንት - አባል

25.የክልሉ ሴቶች ፌዴሬሽን ኘሬዝዳንት - አባል

26.እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ወይም በሰብሳቢው ውሣኔ ሌሎችም መ/ቤቶች ወይም ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 3.2 <u>የክልል ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ኃላፊነትና ተግባር</u>

<u>የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ም/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት አሉት፡፡</u>

- የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ በክልሉ የሚካሄዱትን የሥነ-ሕዝብ ነክ ሥራዎች ሁሉ በበላይነት ያስተባብራል ፣ይመራል፣
- በክልሉ የሚካሄዱትን የሥነ-ሕዝብ እንቅስቃሴዎች በሁሉም አካላት አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም እንዲዘጋጅ ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶች አመራር ይሰጣል፣ የተዘጋጀውን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ከአግባብነቱ አንፃር በመፈተሽ ያፀድቃል፣የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም አስፈጻሚ የሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችና (ድርጅቶች) በሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም መሠረት በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካትተው እንዲተገብሩት ያደርጋል፡፡

- የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አተገባበር ችግር ከገጠመው ጉዳዩን አጥንቶ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ውስጥ ባለው ዕቅድ መሠረት እያንዳንዱ ፈጻሚ መ/ቤት /ድርጅት/ በስትራቴጂክና በአመታዊ ዕቅዱ ውስጥ ማካተቱንና መተግበሩን በየአመቱ መጨረሻ ላይ የአፈጻጸም ሪፖርት መርምሮ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል፡፡
- ከእያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤት ወይም ድርጅት የተውጣጣ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም አመራር ይሰጣል፡፡
- ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ለመተግበር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ አዋጆችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
- ለክልል ምክር ቤትና ለብሔራዊ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በየአመቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## *3.3 በዞኖች እና በሀዋሣ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አወቃቀር*

የዞኖች እና የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ወይም በከተማው አስተዳደር ከንቲባ የሚመራ ሲሆን የፋ/ኢ/ልማት መምሪያም ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

**የዞኖች/ሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት**

1. የዞን ዋና አስተዳዳሪ/ ከንቲባ - ሰብሳቢ
2. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ኃላፊ - ፀሐፊ
3. የጤና መምሪያ ኃላፊ - አባል
4. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መ/መ/ሴክሬታሪያት ኃላፊ- አባል
5. የትምህርት መምሪያ ኃላፊ - አባል
6. የግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ ኃላፊ - አባል
7. የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ - አባል
8. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ - አባል
9. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ - አባል
10. በዞኑ /በከተማው የሚገኝ አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ኃላፊ - አባል
11. የዞኑ/ የከተማ መስተዳድር ም/ቤት አፈ- ጉባዔ - አባል
12. የዞን/ የሀዋሣ አቀፍ የኢትዮጵያ አ/ተ/ቤ/ክ/ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል

13.የዞን/ የሀዋሣ ከተማ አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ህብረት ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል

14.የዞን/ የሀዋሣ ከተማ አቀፍ የሀዋሪያት ቤ/ክ/ጽ/ቤት ኃላፊ- አባል

15.የዞን/የሀዋሣ ከተማ አቀፍ የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ- አባል

16.የዞን/የሀዋሣ ከተማ አቀፍ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤ/ክ/ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል

17.የዞን/የሀዋሣ ከተማ አቀፍ የሴቶች ፌዴሬሽን ሊ/መንበር - አባል

18.የዞን/የሀዋሣ ከተማ አቀፍ የወጣቶች ፌዴሬሽን ሊ/መንበር- አባል

19.በዞኑ/ በከተማው የሚገኙ ከሥነ-ህዝብ ሥራዎች ጋር በተያያዘ አንጋፋ የሆኑ ከ3 ያልበለጡ መያድዎች ኃላፊዎች - አባል

<u>***ማሳሰቢያ፡-***</u> በዞኑ/ በከተማው ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ወይም ሰብሳቢ ውሣኔ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አካላት ወይም መ/ቤቶችም አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

## 3.4 የዞኖች /የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነሕዝብ ምክር ቤት ተግባርና ሀላፊነት

**<u>የሥነ-ሕዝብ ም/ቤቱ ተጠሪነቱ ለዞን/ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊትና ተግባራት ይኖሩታል</u>**

- የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ በዞኑ /በከተማ አስተዳደሩ የሚካሄዱ ሥነ-ሕዝብ ነክ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል።
- በዞኑ /በከተማ አስተዳደሩ የሚካሄዱትን የሥነ-ሕዝብ እንቅስቃሴዎች በሁሉም አካላት አማካይነት አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል የዞኑን/የሀዋሣ ከተማን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ሰነድ እንዲዘጋጅ ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶች /ድርጅቶች/ አመራር ይሰጣል፣ የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራሙ ሲዘጋጅም ከአግባብነቱ አንፃር ፈትሾ ያፀድቃል፣ የፀደቀውን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ሴክተር መ/ቤቶችና ድርጅቶች በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካትተው እንዲተገብሩት ያደርጋል።
- በዞኑ /በከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አፈጻጸም ችግር ከገጠመው ሁኔታውን አጥንቶ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል።
- እያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ፈጻሚ መ/ቤት (ድርጅት) በስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅዱ ውስጥ በሥነ-ሕዝብ ኘሮግራሙ ዕቅድ መሠረት መካተቱንና መተግበሩን በየዓመቱ መጨረሻ ላይ በሚቀርብለት የአፈጻጸም ሪፖርት መሠረት መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል።

- ከእያንዳንዱ ከሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የተውጣጣ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም አመራር ይሰጣል፡፡
- ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን ለመተግበር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
- ለዞኑ/ከተማ አስተዳደር ምክር ቤትና ለክልል ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በየዓመቱ መጨረሻ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## *3.5 በልዩ ወረዳ ፣በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አወቃቀር*

የወረዳ/ የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ/ ከንቲባ የሚመራ ሆኖ የወረዳው /የከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

### *የልዩ ወረዳ ፣የወረዳና የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት*

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ /የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ - ሰብሳቢ
2. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ - ፀሐፊ
3. የጤና ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል
4. የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል
5. የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል
6. የወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል
7. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ- አባል
8. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል
9. በልዩ ወረዳ/በወረዳው/ከተማ አስተዳደሩ የሚገኝ አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ኃላፊ - አባል
10. የልዩ ወረዳ/የወረዳ የከተማ መስተዳድር ም/ቤት አፈ- ጉባዔ - አባል
11. የልዩ ወረዳ/የወረዳና ከተማ አስተዳደር አቀፍ የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ/ጽ/ቤት ኃላፊ - አባል

12.የልዩ ወረዳ/የወረዳ ከተማ አስተዳደር አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ህብረት ጽ/ቤት ኃላፊ-አባል

13.የልዩ ወረዳ/የወረዳ ከተማ አስተዳደር አቀፍ የሀዋሪያት ቤ/ክ/ጽ/ቤት ኃላፊ- አባል

14.የልዩ ወረዳ/የወረዳ ከተማ አስተዳደር አቀፍ የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ- አባል

15.የልዩ ወረዳ/የወረዳ ከተማ አስተዳደር አቀፍ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤ/ክ/ጽ/ቤት ኃላፊ- አባል

16.የልዩ ወረዳ/የወረዳ ከተማ አስተዳደር አቀፍ የወጣቶች ፌዴሬሽን ሊ/መንበር - አባል

17.የልዩ ወረዳ/የወረዳ በከተማው አስተዳደር የሚገኙ ከሥነ-ህዝብ ሥራዎች ጋር በተያየዘ አንጋፋ የሆኑ ከ3 ያልበለጡ መያድዎች - አባል

*ማሳሰቢያ፡-*በልዩ ወረዳ/ በወረዳውና በከተማ አስተዳደር ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ውሣኔ እንደየአስፈላጊነቱ ሌሎች አካላት ወይም መ/ቤቶችም አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## *3.6 የልዩ ወረዳ ፣የወረዳና የከተማ አስተዳደር ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ተግባርና ሀላፊነት*

የሥነ-ሕዝብ ም/ቤት ተጠሪነቱ ለልዩ ወረዳው፣ ወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

- የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ በወረዳው /በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፡ ያስተባብራል፡፡
- በወረዳው/ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በሁሉም አካላት የሚካሄዱትን የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል የወረዳው /የከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ሰነድ እንዲዘጋጅ ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶች (ድርጅቶች) አመራር ይሰጣል፣ የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ሰነዱን ያፀድቃል፣ በፀደቀው የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ሰነድ መሠረት የሚመለከታቸው የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ፈጻሚ መ/ቤቶች/ድርጅቶች በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካትተው እንዲተገብሩት ያደርጋል፡፡

- በወረዳው/በከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አፈጻጸም ችግር ከገጠመው ሁኔታውን አጥንቶ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- እያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ፈጻሚ መ/ቤት (ድርጅት) የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በስትራቴጂክና በዓመታዊ እቅዱ ውስጥ መካተቱንና መተግበሩን በየአመቱ መጨረሻ ላይ በሚቀርብለት የአፈጻጸም ሪፖርት መሠረት መርምሮ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል፡፡
- ከእያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤት ወይም ድርጅት የተውጣጣ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም አመራር ይሰጣል፡፡
- ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን ለመተግበር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
- ለወረዳው/ለከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት እንዲሁም ለዞኑና ለክልሉ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በየአመቱ መጨረሻ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## *<u>ክፍል አራት</u>*

## 4. የሥነ- ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር፣ተግባርና ኃላፊነት

### 4.1 የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ

#### 4.1.1 <u>የክልሉ ሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር</u>

የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በፋ/ኢ/ልማት ቢሮ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት ሲሆን ፀሐፊው ከአባላቱ ውስጥ በሰብሳቢው የሚመረጥ ሆኖ አባላቱ ደግሞ የስነ-ህዝብ ጉዳይን በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው ከሚተገብሩ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶችና ድርጅቶች ወክለው የላኩአቸው ባለሙያዎች ይሆናሉ፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እስካልተፈጠረና ሥራው ካልተስተጓጐለ በስተቀር የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ውክልና እንደቋሚ ውክልና ይቆጠራል፡፡

*<u>የክልል የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት</u>*

1. በክልሉ ፋ/ኢ/ልማት ቢሮ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት - ሰብሳቢ
2. የክልሉ ጤና ቢሮ ተወካይ - አባል
3. የክልሉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ተወካይ -አባል

4. የክልሉ ትምህርት ቢሮ ተወካይ -አባል

5. የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ተወካይ - አባል

6. የክልሉ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ተወካይ -አባል

7. የክልሉ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ተወካይ - አባል

8. የክልሉ ወጣቶችና ጉዳይ ቢሮ ተወካይ - አባል

9. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ተወካይ - አባል

10. የሀዋሣ ዩኒቨርስቲ ተወካይ -አባል

11. የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኀበር ደቡብ ሪጅን /ተወካይ - አባል፡

12. የተቀናጀ የቤተሰብ ጤና አገልግሎት ተወካይ -አባል

13. አይ.ፖስ. የኢትዮጵያ ደቡብ ቅርንጫፍ ተወካይ -አባል

14. ኢንጀንደር ሄልዝ ደቡብ ቅርንጫፍ ተወካይ -አባል

15. የኤፍ.ኤች.አይ. ተወካይ -አባል
16. የወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ -አባል
17. የሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ -አባል

## *4.1.2 <u>የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>*

የክልሉ የሥነሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልሉ ስነ-ሕዝብ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

- የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶችና ድርጅቶችን በመወከል በክልሉ በተለያዩ አካላት አማካይነት በተቀናጀ ሁኔታ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን ለመሥራት እንዲቻል ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ ስልቶችን በጋራ ይቀይሳል፣ ተግባራቱንም ይከታተላል፡፡
- በሁሉም የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አጋር መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተግባራዊ የሚሆን የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም ዶክመንት በማዘጋጀትና በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ በማስፀደቅ ተግባራዊ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፣
- የክልሉ ሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም የእኩሌታ ጊዜ ግምገማ (Mid-Term Evaluation) እና የፍጻሜ ጊዜ ግምገማ (Terminal Evaluation) በማድረግ ለቀጣይ አካሄድ አቅጣጫን ያስቀምጣል፣

- የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በየሴክተር መ/ቤታቸው የልማት ዕቅድ ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን ለማካተትና ለመተግበር በዋናነት ጉዳዩን የሚከታተል ባለሙያ (Focal Person) ሆነው ያገለግላሉ ፤
- እያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባል በመ/ቤቱ ወይም በድርጅቱ የሚከናወኑ ሥራዎች የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ያቀርባል፣
- በክልሉ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትና በክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚሰጡ ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ያከናውናል፣

## 4.2. *የዞንና የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር፣ ተግባርና ሀላፊነት*

### 4.2.1. የዞንና የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር

የዞንና የሀዋሣ ከተማ  አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት (አስተባባሪ) ሲሆን ፀሐፊው ከአባላቱ ውስጥ በሰብሳቢው የሚመረጥ ሆኖ አባላቱ ደግሞ ሁሉም የዞኑ/ሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶችና ድርጅቶች የወከሏቸው ባለሙያዎች ይሆናሉ፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እስካልተፈጠረና ሥራው በተወካዩ ካልተስተጓጐለ በስተቀር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ውክልና እንደቋሚ ውክልና ይቆጠራል፣

<u>*የዞን/ የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት*</u>

1. በፋ/ኢ/ልማት መምሪያ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ወሳኝ የሥራ ሂደት ባለቤት ( አስተባባሪ )- ሰብሳቢ
2. የጤና መምሪያ ተወካይ - አባል
3. የኤች.አይ.ቪ/ኤድ መ/መ/ሴክሬታሪያት ተወካይ - አባል
4. የትምህርት መምሪያ ተወካይ -አባል
5. የግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ ተወካይ - አባል
6. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ  መምሪያ ተወካይ - አባል
7. የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ተወካይ - አባል
8. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች  መምሪያ ተወካይ - አባል

9. በዞኑ/በሀዋሣ ከተማ አስተዳደር  ከፍተኛ የትምህርት ተቋም  ተወካይ -አባል
10. በዞኑ/በሀዋሣ ከተማ አስተዳደር  በሥነ-ሕዝብ ነክ ሥራዎች ዙሪያ አንጋፋ የሆኑ የስነ-ህዝብ ምክር ቤት አባል የሆኑ  መያዶች ( መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቶች ) ተወካዮች- አባል /አባላት/
11. የወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ - አባል
12. የሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ - አባል

4.2.2 ***የዞን/ሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት***

የዞኑ ወይም የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞኑ / ለከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣፣

1. የዞኑ/የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን በመወከል፣በዞኑ/በሀዋሣ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ አካላት አማካይነት የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ ለመሥራት እንዲቻል ሙያዊና ቴክኒካዊ ዕገዛ ያደርጋል፣ስልቶችን በጋራ ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
2. በሁሉም በሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አጋር መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተግባራዊ የሚሆን የዞኑን /የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም በማዘጋጀትና በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ በማስፀደቅ ተግባራዊ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፣
3. የዞኑን/ከተማ አስተዳደረን ሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም የእኩሌታ ጊዜ ገምገማ (Mid-Term Evaluation) እና የፍጻሜ ጊዜ ግምገማ (Terminal Evaluation) በማድረግ ለቀጣይ አካሄድ አቅጣጫን  ያስቀምጣል፣
4. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በየሴክተሩ መ/ቤታቸው የልማት ዕቅዶች ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን ለማካተትና ለመተግበር አመቻች ወይም በዋናነት ጉዳዩን የሚከታተል ባለሙያ (Focal Person) ሆነው ያገለግላሉ፣
5. እያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባል በመ/ቤቱ ወይም በድርጅቱ የሚከናወኑ ሥራዎች የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ለዞኑ/ ለሀዋሣ ከተማ አስተዳደር ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ያቀርባል፣
6. በዞኑ/በከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የሚሰጡ ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትንም ያከናውናል።

## 4.3 *የልዩ ወረዳ /የወረዳ /የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር ፣ተግባርና ሀላፊነት*

### 4.3.1 የልዩ ወረዳ /የወረዳ /የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ኮሚቴ አወቃቀር

የልዩ ወረዳው /የወረዳው/ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት ( አስተባባሪ ) ሲሆን ፀሐፊው ከአባላቱ ውስጥ በሰብሳቢው የሚመረጥ ሆኖ አባላቱ ደግሞ የልዩ ወረዳው/ ወረዳው/ የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶችና ድርጅቶች እንዲወክሉአቸው የላኩአቸው ባለሙያዎች ይሆናሉ፡፡

ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልተፈጠረና ተወካዩ ሥራውን በአግባቡ ካልተወጣ በስተቀር የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ውክልና እንደቋሚ የሚቆጠር ነው፡፡

*የልዩ ወረዳ /የወረዳ /የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት*

1. በፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት ( አስተባባሪ ) - ሰብሳቢ
2. የጤና ጽ/ቤት ተወካይ - አባል
3. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ተወካይ - አባል
4. የትምህርት ጽ/ቤት ተወካይ -አባል
5. የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ተወካይ - አባል
6. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት ተወካይ - አባል
7. የወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ተወካይ - አባል
8. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ተወካይ - አባል
9. የልዩ ወረዳ/የወረዳ/ የሀዋሣ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተወካይ - አባል
10. በሥነ-ሕዝብ ነክ ሥራዎች ዙሪያ በግምባር ቀደምትነት የሚሠሩ የስነ-ህዝብ ም/ቤት አባል የሆኑ (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ተወካዮች - አባል /አባላት/ ናቸው፡፡
11. የወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ - አባል
12. የሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ - አባል

4.3.2 <u>የልዩ ወረዳ /ወረዳ/ የከተማ አስተዳደር/ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የልዩ ወረዳው /የወረዳው/ የከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

- የልዩ ወረዳው /የወረዳው የከተማ/ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መ/ቤቶችና ድርጅቶችን በመወከል በልዩ ወረዳው /በወረዳው/ በከተማ አስተዳደር በተለያዩ አካላት አማካኝነት በተቀናጀ ሁኔታ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን በተሳካ ሁኔታ ለመሥራት እንዲቻል ሙያዊና ቴክኒካዊ ዕገዛ ያደርጋል፣ ስልቶችን በጋራ ይቀይሣል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።
- በሁሉም የሥነ-ሕዝብ አጋር መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተግባራዊ የሚሆን የልዩ ወረዳውን/ወረዳውን/ የከተማ አስተዳደሩን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም በጋራ ማዘጋጀትና በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቱ በማስፀደቅ ተግባራዊ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፣
- የልዩ ወረዳውን/የወረዳውን /የከተማ አስተዳዳሩን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም የእኩሌታ ጊዜ ግምገማ (Mid Term Evaluation) እና የፍጻሜ ጊዜ ግምገማ (Terminal Evaluation) በማድረግ ለቀጣይ አካሄድ አቅጣጫን ያስቀምጣል።
- የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በየሴክተር መ/ቤታቸው የልማት ዕቅዶች ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን ለማካተትና ለመተግበር በዋናነት ጉዳዩን የሚከታተል ባለሙያ ( Focal Person ) ሆነው ያገለግላሉ።
- እያንዳንዱ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባል በመ/ቤቱ ወይም በድርጅቱ የሚከናወኑ ሥራዎች የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤትና ለልዩ ወረዳው /ለወረዳው/ ለከተማ አስተዳደሩ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ያቀርባል።
- በልዩ ወረዳው /በወረዳው /በከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተንዳኝ ተግባራትንም ያከናውናል።

**ይህ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የስነ-ህዝብ ም/ቤትና የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋሚያ የአፈፃፀም መመሪያ በክልሉ ስነ-ህዝብ ም/ቤት ህዳር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ፀድቋል።**

**ህዳር 2002 ዓ.ም**

**<u>ሀዋሣ</u>**